ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሮማን ደምሴ

*የስራ ክርክር - ይርጋ - አላግባብ ተቋርጧል የተባለን የስራ ውል ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ - የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1)*

አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ወይ ስራዋ እንድትመለስ እና ጥቅማ ጥቅሞቹ እንዲጠበቁለት በማለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር የሠጡትን ውሳኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

__ው ሳ ኔ__ ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1ኛ. የስራ መደብ ያልተቋረጠ ከሆነ ወደ ስራ ልመለስም ሆነ የውል አበል ክፍያ ይገባኛል የሚል ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ድንጋጌ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡

2ኛ. አንድ ሠራተኛ ከስራና ከደመወዝ ከዘጠና ቀን በላይ ከታገደ የስራ መቋረጡ ባይገለፅለትም መብቱን ለመጠየቅ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው የዕግድ ጊዜ ከሚያበቃበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡





ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ገጠር መንገች ባለሥልጣን - ሰላማዊት ኃይሉ ቀረበች
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሮማን ደምሴ - ቀረበች

__ፍ ር ድ__

ይህ ጉዳይ ዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሠረተችው ክስ የተጀመረ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች ከሕዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ጥር ወር 1993 ዓ.ም ድረስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንድውል ከአስደረገ በኋላ ኦዲት ይደረግና ትመለሻለሽ በሚል ከስራና ከደመወዝ አግኛል፡፡ ይሁን እንጂ ከሚያዝያ 23 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የኦዲቱ ስራ የተከናወነ ቢሆንም ስራዬ ላይ ግን ሊመልሰኝ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም የውሉ አበሌን ከፍሎ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም ክሱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ስለሆነ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162/1/ መሠረት በይርጋ ይታገድልኝ የሚል መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳዩም አለኝ የሚለውን መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የተጠሪ የስራ ውል መቼ እንደተቋረጠ ባይታወቅም ክሱ የተመሠረተው ግን ኦዲት ተደርጎ ትመለሻለሽ ተብያለሁ ከአለችበት እለት ከጥር ወር 1993 ዓ.ም በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ ማለትም ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ነው እንዲሁም ተጠሪ አመልካቹ መብቱን አውቆልኛል ብትልም ለዚህ ያቀረበችው የጽሁፍ ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም ሌላ የቆጠረቻቸው የሰው ማስረጃዎችም ያላስረዱላት በመሆኑ የይርጋው አቆጣጠር ሊቋረጥ የሚችል አልሆነም ስለሆነም ክሱ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አንድ የስራ ውል የሚቋረጠው በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 27(2) መሠረት አሰሪው ለሰራተኛው በሚሰጠው ጽሁፍ መሆን ሲገባው ይኸ በአመልካቹ አልተደረገም፡፡ ስለሆነም በሁለቱ መካከል የተፈፀመው የስራ ውል ስላልተቋረጠ አመልካቹ ለተጠሪዋ መሰጠቱ ከቆመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ደመወዝዋን ከፍሎ ወደ ስራዋ ሊመልሣት ይገባል በማለት ወስኖ የስር ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በውሣኔው የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ይህም ችሎት በግራ ቀኙ የቀረበለትን ክርክር መርምሯል፡፡ ምላሽ የሚያስፈልገውም የጉዳዩ ነጥብ በተጠሪ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊተገድ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? የሚለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡ የተያዘውን ጭብጥ ለመፍታት በቅድሚያ ጉዳዩ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162 ስር ከተመለከቱት የይርጋ ደንቦች ውስጥ ከየትኛው ንዑስ አንቀጽ አግባብ ሊታይ እንደሚገባው መለየት ያስፈልጋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካቹ ተጠሪዋ በእጅዋ ከገባው ገንዘብ ውስጥ ብር 21.595.00 አጉድላ ለግል ጥቅምዋ ማዋሏ ተረጋግጧል ቢልም ይህን ምክንያት ጠቅሶ የስራ ውሏን አለማቋረጡን አልካደም፡፡ ክርክሩ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ከዋለችበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ የስራ ውሏ ተቋርጧል ሊሰኝ ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በሁለቱ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት በሕግ መቋረጡን ስለማያመለክት ውሉ አልተቋረጠም ሲል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ሊነቀፍ የሚገባው አልሆነም፡፡ የስራ ውሉ ያልተቋረጠ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ ይገባል ስትል ያቀረበችው የክሷ ነጥብም ሆነ የውሎ አበል ክፍያ ይገባኛል ስትል ያነሣችው ጥያቄ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) ስር ከተመለከተው አጠቃላይ የይርጋ ደንብ ድንጋጌ አኳያ እንጂ በተለይ ከተደነገጉት ንዑስ አንቀጽ (2) እና (4) አግባብ ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከስራ እና ከደመወዝ ከኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ታግዳ የቆየች መሆኑን አልካደችም፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ግንቦት 14 ቀን



1994 ዓ.ም ድረስ ሒሣብ እያስመረመርኩ ስለሆነ ስራ ላይ እንደነበርኩ ሊቆጠርልኝ ይገባል በሚል አይነት ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በሒሣብ ማስመርመር ተግባር ላይ መቆየቷ ግን መደበኛ ስራዋን ስታከናውን ነበር የሚያሰኛት ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረበችው ክርክር አሣማኝነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከስራና ከደመወዝ የታገደችበት እለት ኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም መሆኑን ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

እንግዲህ ከፍ ሲል እንደመለከተው ተጠሪ የስራ ውሏ መቃረጥ በአመልካቹ ባይገለጽላትም ከኅዳር 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ከስራና ከደመወዝ መታገድዋ ግን ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከዘጠና ቀናት በላይ ከስራና ከደመወዝ ሊታገድ እንደማይችል ደግሞ ከአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 21(1) መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ሕጉ ለእግድ የፈቀደው ጊዜ እንደአበቃ ይገባኛል የምትለው ነገር በአመልካቹ ካልተደረገላት መብቷን ክስ መስርታ ትጠይቅ ዘንድ ይገባል፡፡ ክሷን የምትመሰርተውም በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት ጥያቄዋን ልታቀርብ ከምትችልበት ማለትም የእግዱ ጊዜ ከማደበቃበት ከየካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ማለትም እስከ የካቲት 14 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ብቻ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

አመልካች ግን ክሷን የመሠረተችው ጥቅምት 19 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የተጠቀሰውን የአንድ ዓመት የይርጋ ጊዜ አሳልፎ የቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## ው ሣ ኔ

1ኛ. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተችው ክስ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 162(1) መሠረት በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል፡፡

2ኛ. የዓለም ገና ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.63/95 ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠው ውሣኔ ፀንቶ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ደኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመ.ቁ. 02006 እና 16113 ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡